# ለኢንቨስትመንት ኘሮጀክቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን እንደገና ተሻሽሎ

## የወጣው መመሪያ

እንደ ኢንቨስትመንት ኘሮጀክቶች ዓይነትና ባሕሪ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ እንደሚወሰን በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 84/1995 አንቀጽ 9 የተደነገገ ስለሆነ፣

በዚህም መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው ስለሚገቡ ተሽከርካሪዎች አፈቃቀድ ቦርዱ በ1997 የተሻሻለ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ያደረገ በመሆኑ፣

ኢንቨስትመንትን ይበልጥ ለማበረታታት እና ለማስፋፋት ተሽከርካሪዎች ያለ ጉምሩክ ቀረጥ እንዲገቡ የሚፈቀድባቸውን ሁኔታዎች ምንደገና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢንቨስትመንት ቦርድ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/94 /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 29/3 እና በደንቡ አንቀጽ 9 መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል 1 ጠቅላላ

## አንቀጽ1 የሚፈቀድ-

## አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ስለተፈቀደበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እንደገና ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 2/1999ዓ/ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2/ አንቀጽ 2

## ትርጉሜ

በዚህ መመሪያ፡-

1/ «ተሽከርካሪ» የሚለው ቃል ደረቅና ፈሳሽ ጭነት መኪናዎችን፣ ሞተር ብስክሌትን፣ ፒክ-አኘ ፎርዊል ድራይቭን ፣ የሠራተኛ ማጓጓዣ አውቶቡስን /ሚኒባስን ብቻ የሚያካትት ነው፡፡

2/ «ደንብ» ማለት ስለ ኢንቨስትመንት ማበረታቻና ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 84/1995 ዓ/ም ነው፡፡

3/ «ሎጅ» ማለት ብሔራዊ ፓርኮችን ወይም ታሪካዊ ቦታዎችን ለመጎብኘት ወይም በሌሎች የቱሪዝም መስሕብ ቦታዎች ለመዝናናት ለሚመጡ እንግዶች የምግብ እና የማደሪያ አገልግሎት ለመስጠት ፓርኩን ወይም ታሪካዊ ቦታውን ወይም የቱሪዝም መስሕቡን ከሚያስተዳድረው አካል ጋር በተደረገ ስምምነት ወይም በተሰጠው ዕውቀትና በፓርክ ወይም በታሪካዊ ቦታዎች ክልል ወይም በቱሪዝም መስሕብ ቦታዎች ውስጥ ወይም ዳር ላይ የሚቋቋም አገልግሎት ሰጪ ተቋም ነው፡፡

## ክፍል II

## በተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድላቸው የሥራ መስኮችና የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት

### 3/ አንቀጽ

### ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የማስገባት ማበረታቻ የሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት መስኮች

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 የተደረገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት ማበረታቻ የሚሰጠው ለማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ ግብርና፣ለቱሪዝም፣ ለኮንስትራክሽን፣ ለውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፣ ለምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ግንባታ እንዲሁም ለልዩ ሥራ ተቋራጭነት የኢንቨስትመንት መስኮች ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ለተመለከቱት የኢንቨስትመንት መስኮች እና ማበረታቻ ለሚፈቀድላቸው ሌሎች የኢንቨስትመንት መስኮች ለሠራተኞች ማጓጓዣ የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ይፈቀዳል፡፡

### 4/ አንቀጽ 4

### ለማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1/ በዚህ መመሪያ በአባሪ ፊደል ተራ ,ሀ,፣,ለ, እና ,ሐ, ከተዘረዘሩት ልዩ ትኩረት ከሚሰጣቸው የማምረቻ ኢንዱስትሪ የሥራ መስኮች መካከል በአንዱ የተሰማራ ባለሀብት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገባ የሚፈቀድለት የተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተመለከተው በፕሮጀክቱ የኢንቨስትመንት ካፒታል መጠን ይሆናል፡፡

ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ለተመለከቱት የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የሚፈቀዱት ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

| ተ.ቁ | ለኢንቨስትመንት የታፈቀደው የካፒታል መጠን | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ከ3እስከ 15 ሚሊዮን ብር | 1 ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት መኪና<br>ፒክ አኘ (4WD) |
| 2 | ከ15 ሚሊዮን ብር በላይ እስከ 30 ሚሊዮን ብር | 1 ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት መኪና ወይም 2 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች 2 ፒክ አኘ(4WD) |
| 3 | ከ30 ሚሊዮን ብር በላይ እስከ 45 ሚሊዮን ብር | 1 ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት መኪና<br>1 ከ5-10ቶን የሚጭን የጭነት መኪና ወይም 2 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች 2 ፒክ አኘ (4WD) |
| 4 | ከ45 ሚሊዮን ብር በላይ እስከ 60 ሚሊዮን ብር | 2 ከ5-10 ቶን ወይም 4 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች<br>3 ፒክ አኘ (4WD) |
| 5 | ከ60 ሚሊዮን ብር በላይ እስከ 500 ሚሊዮን ብር | 2 ከ5-10 ቶን ወይም 4 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች<br>1 ከ3-5ቶን የሚጭን የጭነት መኪና<br>3 ፒክ አኘ (4WD) |

3/ በዚህ መመሪያ በአባሪ ተራ ፊደል ,ሀ, ፣ ,ለ, እና, ሐ, ከተዘረዘሩት የማምረቻ ኢንዱስትሪ የሥራ መስኮች መካከል በአንዱ የሚሰማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀው ባለሀብቱ፡-

ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ /የፋብሪካ ሕንፃ ተከራይቶም ከሆነ ሕጋዊ የኪራይ ውል/ ማስረጃ፣

ለ/ ኘሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት መሠረተ ልማት ፣መጋዘን እና መንገድ የመሣሠሉት እየተሠሩ ስለመሆናቸው ኘሮጀክቱ ካለበት የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ማስረጃ ፣

ሐ/ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሌዲንግ(Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል(Airway Bill) ወይም ትራዌይ ቢል (Truck way Bill) እና የግዢ ደረሰኝ (invoice) ሲቀርብ ወይም የካፒታል ዕቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግዢውን ውል ከአስፈላጊ ማስረጃዎች ጋር እና

መ/ ባለሀብቱ የፋብሪካ ሕንፃ ተከራይቶ የሚሠራ ከሆነ የመሣሪያ ተከላ ስለመጀመሩ ፕሮጀክቱ ካለበት የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ማስረጃ፣ የጉምሩክ ቀረጥ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡

4/ በዚህ መመሪያ በአባሪ ተራ ፊደል, ሀ፣, ለ, እና, ሐ, ከተዘረዘሩት ውጭ ባሉ የማምረቻ ኢንዱስትሪ የሥራ መስኮች የተሠማራ ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት ጥያቄ ሲያቀርብ ጥያቄው ለቦርድ እየቀረበ ይወሰናል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ 4 መሠረት ባለሀብቱ ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት ሲጠይቅ ለኢንቨስትመንቱ የታቀደው የካፒታል መጠን ቢያንስ 10 ሚሊዮን ብር መሆኑን የሚገልፅ እና በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 3 የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

6/ አንድ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቆ የማምረት ሥራ ሲጀምር ኢንቨስት ያደረገው የካፒታል መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 የተመለከተው መጠን የተሟላ ስለመሆኑ የንብረት ዋስትና ኢንሹራንስ የገባበት ወይም የባንክ ብድር እና/ወይም የራስ ገንዘብ ወጪ ማስረጃዎቹን የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለፈቀደው አካል ማቅረብ ያለበት ሲሆን፣ መጠን ከተመለከተው በታች ሆኖ ከተገኘ በኢንቨስትመንት አዋጁ /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 18 መሠረት አስፈላጊው ሕጋዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

## አንቀጽ 5

## ለግብርና ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1/ በግብርና ሥራ መስክ የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 በተገለፀው መሠረት በሚያለማው የመሬት ስፋት ፣ በሚኖረው የእንስሳት ብዛት፣ የቀፎ ብዛት እና የሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሀብቱ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት፣

ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ ወይም ተከራይቶም ከሆነ የኪራይ ውል ማስረጃ ፣

ለ/ የኘሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት መሠረተ ልማት ፣ መጋዘን እና መንገድ የመሣሠሉት እየተሠሩ ስለመሆናቸው ኘሮጀክቱ ከሚገኝበት ክልል የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ማስረጃ ፣ እና

ሐ/ ለኘሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ስለመገዛታቸው ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Air way Bill ወይም ትራክዌይ ቢል (Truck way Bill) እና የግዢ ደረሰኝ (invoice) ወይም የካፒታል ዕቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግዢውን ውል ከአስፈላጊ ማስረጃዎች ጋር፣ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡

3/ አንድ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቆ የማምረት ሥራ ሲጀምር ያለማው የመሬት ስፋት ወይም ያለው የእንስሳት ብዛት ወይም የቀፎ ብዛት ወይም የሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 የተመለከተው መጠን የተሟላ ስለመሆኑ ፈቃድ ከሰጠው የኢንቨስትመንት አካል ማስረጃውን የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለፈቀደው አካል ማቅረብ ያለበት ሲሆን፣ መጠን ከተመለከተው በታች ሆኖ ከተገኘ በኢንቨስትመንት አዋጁ /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 18 መሠረት አስፈላጊው ሕጋዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

**ለእርሻ ልማት ኢንቨስትመንት ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀደው ከዚህ በታች በተገለፀው ሠንጠረዥ መሠረት ነው፡፡**

| ተ.ቁ | የሥራ መስክ | የሚለማው የመሬት ስፋት በሄክታር | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | የብርዕ፣የአገዳ እና/ወይም የጥራጥሬ እህሎች ልማት፣ የቅባት እህሎች፣እና/ወይም ተክሎች ልማት | ከ40-150 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ151-300 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌት<br>1 ከ5-10ቶን የሚጭን የጭነት መኪና ወይም 2 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |
| | | ከ301-450 | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌቶች<br>2 ከ5-10ቶን ወይም 4 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |
| | | ከ450 በላይ | 3 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌቶች<br>2 ከ5-10ቶን ወይም 4 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |
| 2 | የአትክልት፣የፍራፍሬና የቅመማ ቅመሞች ልማት | ከ10-50 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ51-100 | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>1 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪና |
| | | ከ101-150 | 3 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>1 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪና |
| | | ከ150 በላይ | 3 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌት<br>2 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |
| 3 | የቡና፣ የሻይ እና የመሳሰሉት አንቂ ተክሎች ልማት | ከ20-80 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>1 ከ3-5ቶን የሚጭን የጭነት መኪና |
| | | ከ18-150 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>1 ከ5-10ቶን የሚጭን የጭነት መኪና ወይም 2 ከ3-5 ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |
| | | ከ151-250 | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌቶች<br>1 ከ3-5ቶን የሚጭን የጭነት መኪና<br>1 ከ5-10ቶን የሚጭን የጭነት መኪና ወይም 2 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |
| | | ከ250 በላይ | 3 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌቶች<br>1 ከ3-5ቶን የሚጭን የጭነት መኪና<br>2 ከ5-10ቶን የሚጭኑ ወይም 4 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |

ድንች መሰል የሥራ ሥር ተክሎች እና ዕፀ ጣዕምን(Herba) ይጨምራል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መስክ | የሚለማው የመሬት ስፋት በሄክታር | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|---|---|
| 4 | የአዝርዕት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እና ይአንቂ ተክሎች ምርጥ ዘሮች ልማት | ከ2-5 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ6-10 | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ11-20 | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌቶች<br>1 ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት መኪና |
| | | ከ20 በላይ | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌቶች<br>2 ከ3-5 ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |
| 5 | የእንስሳት መኖ ሰብል ልማት | ከ80-150 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ151-300 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌቶች<br>1 ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት መኪና<br>1 ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት መኪና ወይም 2 ከ3-5 ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |
| | | ከ300 በላይ | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌቶች<br>2 ከ3-10 ቶን ወይም 4 ከ3-5 ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |
| 6 | የጭረት ተክሎች ልማት | ከ50-100 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>1 ከ3-5ቶን የሚጭን የጭነት መኪና |
| | | ከ101-150 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌቶች<br>1 ከ5-10ቶን የሚጭን የጭነት መኪና ወይም 2 ከ3-5 ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |
| | | ከ151-250 | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌቶች<br>1 ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት መኪና<br>1 ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት መኪና ወይም2 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |
| | | ከ250 በላይ | 3 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌቶች<br>1 ከ3-5ቶን የሚጭን የጭነት መኪና<br>2 ከ5-10ቶን ወይም 4 ከ3-5ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |

| ተራ ቁጥር | የሥራ መስክ | የሚለማው የመሬት ስፋት በሄክታር | የተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት |
|---|---|---|---|
| 7 | የአበባና የጌጣጌጥ ተክሎች ልማት | ከ2-10 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ11-20 | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ21-50 | 3 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ51-100 | 4 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ100 በላይ | 5 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌት |
| 8 | የደን ልማት /የጎማ ዛፍ ልማትን ይጨምራል/ | ከ100-300 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>1 ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት መኪና ወይም2 ከ3-5ቶንየሚጭኑ የጭነትመኪናዎች |
| | | ከ301-500 | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>2 ከ5-10 ቶን ወይም 4 ከ3-5 ቶን የሚጭኑ ጭነት መኪናዎች |
| | | ከ500 በላይ | 3 ፒክ አፕ (4WD)<br>2 ሞተር ብስክሌቶች<br>3 ከ5-10 ቶን ወይም 6 ከ3-5 ቶን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች |
| 9 | ፀረ ተባይ ፣ፀረ አረም ፣ፀረ ሻጋታ እና መድሃኒት ለማምረት የሚውሉ ተክሎች ልማት | ከ10-50 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ50 በላይ | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |

5/ ለእንስሳት ሀብት ልማት ኢንቨስትመንት ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀደው ከዚህ በታች በተገለፀው ሠንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

| ተራ ቁጥር | የሥራ መስክ | የፕሮጀክት አቅም በእንስሳት ብዛት ፣ በቀፎ ብዛት እና በሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት | የተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | የዳልጋ ከብት፣ የግመል፣የበግና ፍየል እርባታእና/ ወይም ማድለብ | ከ200-500 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ500 በላይ | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| 2 | የወተት ሀብት ልማት | ከ100-300 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ300 በላይ | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |

* ማድለብ ከሆነ በአንድ ዙር

| ተራ ቁጥር | የሥራ መስክ | የፕሮጀክት አቅም በእንሰሳት ብዛት ፣በቀፎ ብዛት እና በሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት | የተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት |
|---|---|---|---|
| 3 | የዶሮ፣ የቆቅ፣ የጅግራና የመሳሰሉ አዕዋት እርባታ | ከ5,000,10,000 | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ10,001-20,000 | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ20,000 በላይ | 3 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| 4 | የዓሳማ፣የጥንቸል፣ የጥርኝ፣እና መሳሰሉ እንሰሳት ባታ | 200 እና ከ200 በላይ | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| 5 | የአዞ እርባታ | 500 እና በላይ | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| 6 | የሰጎን እርባታ | 200 እና ከ200 በላይ | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| 7 | ንብ ማነብና ማር ማምረት | ከ500-1000 ቀፎ | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ1000 ቀፎ በላይ | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| 8 | የዓሳ እርባታ | ከ1250ሜ. ኩ-2000ሜ.ኩ | 1 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ2000ሜ.ኩ በላይ | 2 ፒክ አፕ (4WD)<br>1 ሞተር ብስክሌት |

## የኮንስትራክሽን ፤የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፣የምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ግንባታ እንዲሁም ልዩ የሥራ ተቋራጭነት ፤

1./ በኮንስትራክሽን ፣ በውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፣ በምሰቦ ጉድጓድ ቁፍሮና ግንባታ እንዲሁም በልዩ ሥራ ተቋራጭነት የተሠማራ ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በተገለፀው መሠረት ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑሰ አንቀጽ 1 በተመለከቱት የሥራ መስኮች የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ባለሀብቱ፡-

ሀ/ የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ለደረጃው እንደሚያስፈልጉ ከዘረዘራቸው መሣሪያዎች በዋጋ ሃያ አምስት በመቶ (25%) ያህሉን ከውጭ ሀገር ስለመግዛቱ ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Airway Bill) ወይም ትራክዌይ ቢል (Truck way Bill) እና የግዥ ደረሰኝ (invoice) ወይም ሌላ የዋጋ ግምት ማረጋገጫ ሰነድ፣ወይም

ለ/ መሣሪያዎቹን ከሀገር ውስጥ የገዛ ከሆነ የግዥ ውሉን ከአስፈላጊ ሠነዶች ጋር& የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

3/ ለውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ለመሠረት ጉድጓድ ቁፋሮና ግንባታ የኢንቨስትመንት መስኮች ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀደው ድሪሊንግ ሪጉ ወይም ጉድጓድ መቆፈሪያው / መሰርሰሪያው የተገዛው ስለመሆኑ ማረጋገጫ እና የማስጫኛ ሠነድ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

ለኮንስትራክሽን ለውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ & ለምሰሶ ጉድጓድ ፣ቁፋሮና ግንባታ እንዲሁም ለልዩ ሥራ ተቋራጭነት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የሚፈቀዱ የተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት የሚወሰነው ከዚህ በታች በተገለፀው ሠንጠረዥመሠረት ነው።

| ተራ ቁጥር | የኮንስትራክሽን ዘርፍ | ደረጃ አንድ | ደረጃ ሁለት | ደረጃ ሦስት | ደረጃ አራት | ደረጃ አምስት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭነት<br>ፒክ አፕ (4WD) | 7 | 6 | 4 | 3 | 1 |
| 2 | የሕንፃ ሥራ ተቋራጭነት<br>ፒክ አፕ (4WD) | 4 | 3 | 2 | 2 | 1 |
| | ከ3-10 ቶን የሚጭን -የጭነት መኪና | 2 | 1 | - | - | - |
| 3 | የመንገድ ሥራ ተቋራጭነት<br>ፒክ አፕ (4WD) | 6 | 5 | 3 | 2 | - |
| 4 | ልዩ ሥራ ተቋራጭነት (ኤሌክትሮ ሜካኒካል ) | 3 | 2 | - | - | - |
| | • ፒክ አፕ (4WD) | 1 | 1 | - | - | - |
| | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት መኪና | | | | | |
| | • ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት መኪና | 1 | 1 | - | - | - |
| 5 | የምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮና ግንባታ ሥራ ተቋራጭነት | ለአንድ መቆፈሪያ /መሰርሰሪያ 2 ፒክ አፕ (4WD) እና 1 ክሬን ትራክ | | | | |
| 6 | የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ተቋራጭነት | ለአንድ ድሪሊንግ ሪግ 2 ፒክ አፕ (4WD) እና 1 ክሬን ትራክ | | | | |

## <u>ለሎጅ ፡ አገልግሎት ኢንቨስትመንቶች</u>
## <u>የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች</u>

1/ **<u>በብሔራዊ ፓርክ ወይም በታሪካዊ ቦታ ክልል</u> ወይም በሌላ የቱሪዝም መስሕብ ቦታ ውስጥ ወይም ዳር ላይ ለሚቋቋም የሎጅ አገልግሎት ኘሮጀክት የሚውል ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚቀርብ ጥያቄ በቦርድ እየታየ የሚወሰን ይሆናል፡፡**

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገባ በባለሀብት ሰጠየቅ፡-

ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ/ ተከራይቶም ከሆነ የኪራይ ውል ማስረጃ፣

ለ/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅሰቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የሕንፃው ግንባታ፣መሠረተ ልማት እና መጋዘን የመሣሰሉት እየተሠሩ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ማስረጃ ፣ እና

ሐ/ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ስለመገዛታቸው ቢል ኦፍ ሌዲግን (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (invoice) ወይም የካፒታል ዕቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገዙ ከሆነም የግዥውን ውል ከአስፈላጊ ማስረጃዎች ጋር ፣ ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 8/ አንቀጽ 8

## የሠራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች

1/ ማበረታቻ ለሚፈቀድለት ማንኛውም ባለሀብት ለሠራተኛ ማጓጓዣ የሚያስፈልገውን ተሽከርካሪ እንደ ፕሮጀክቱ የሠራተኛ ብዛት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ በተመለከተው መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተሽከርካሪን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀደው ባለሀብቱ በቅድሚያ።

ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ/ ተከራይቶም ከሆነ የኪራይ ውል ማስረጃ ፣

ለ/ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል(Airway bill)ወይም ትራክዌይ ቢል(Track way Bill) እና የግዢ ደረሰኝ (invoice)ወይም የካፒታል ዕቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገኙ ከሆነ የግዥ ውል ከአስፈላጊ ሠነዶች ጋር ፣

ሐ/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት፣ የሕንፃ ግንባታ፣መሠረተ ልማት ፣መጋዘን እና መንገድ የመሳሰሉት እየተሠሩ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት የክልል ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ማስረጃ፣እና

መ/ ለፕሮጀክቱ ተቀጥረው በመሥራት ላይ የሚገኙ ሠራተኞችን ሥም ዝርዝር የያዘ የደመወዝ መክፈያ ሠነድ (pay roll) እና ለመንግሥት የደመወዝ ግብ የተከፈለበት ማስረጃ፣ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቀድሙ አካል ሲያቀርብ ነው።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሠራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ የሚፈቀደው ከዚህ በታች በተገለፀው ሠንጠረዥ መሠረት ነው።

| ቋሚ የሠራተኛ ብዛት | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|
| ከ10-12 | 1 ሚኒባስ |
| ከ13-50 | 2 ሚኒባሶች ወይም 1 አውቶቡስ |
| ከ50 በላይ -500 | ለእያንዳንዱ ተጨማሪ 50 ሠራተኛ 1 አውቶቡስ ወይም 1 ሚኒባስ |

## ክፍል III

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌ</u>

### <u>አንቀጽ 9</u> (9)

### <u>በአገር ውስጥ ስለሚገጣጠሙ /ስለሚመረቱ ተሽከርካሪዎች</u>

ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገባ የሚፈቀድለት ባለሀብት ከአገር ውስጥ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ/ማምረቻ ፋብሪካ ተሽከርካሪ ቢገዛ ተሽከርካሪውን ለማምረት ከውጭ ተገዝተው በገቡ የተሽከርካሪው ግብዓቶች ላይ የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ ተሠልቶ ይቀነሳል፡፡

## አንቀጽ (10)

## ከፍተኛ ኢንቨስትመንቶች

1) ከ500 (አምስት መቶ) ሚሊዮን ብር በላይ ኢንቨስት የሚያደርግና በደንቡ መሠረት የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ባለሀብት በዚህ መመሪያ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ከሚፈቀዱለት በተጨማሪ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት ጥያቄ ሲያቀርብ ጥያቄው ለቦርዱ እየቀረበ ይወሰናል ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዕስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም፣ በማበረታቻ ደንቡ መሠረት የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ በነፃ እንዲያስገባ የማይፈቀድለት እና ቢያንስ 500 ሚሊዮን ብር ኢንቨስት የሚያደርግ ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት ጥያቄ ሲያቀርብ ጥያቄው ለቦርድ እየቀረበ ይወሰናል፡

## አንቀጽ (11)

## በአንፃራዊ ደረጃ በኢኮኖሚ ልማት ወደኋላ በቀሩ አካባቢዎች ስለሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች

በዚህ መመሪያ የተመለከተው ቢኖርም በአንፃራዊ ደረጃ በኢኮኖሚ ልማት ወደኋላ በቀሩ አካባቢዎች ኢንቨስት የሚያደርግና በደንቡ መሠረት የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ባለሀብቶች ተጨማሪ የተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት ጥያቄ ሲያቀርብ ጥያቄው ለቦርዱ እየቀረበ ይወሰንለታል ፡፡

## አንቀጽ (12)

## ብስክሌትን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ስለማስገባት

ብስክሌትን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚቀርብ ጥያቄ በቦርድ እየታየ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ (13)

## ተሽከርካሪዎች በመመሪያው ያልተሸፈኑ ኘሮጀክቶች

በዚህ መመሪያ ከተዘረዘሩት የኢንቨስትመንት የሥራ መስኮች ውጭ ለሌሎች የኢንቨስትመንት የስራ መስኮች የተሽከርካሪ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ጥያቄ ሲቀርብ ቦርዱ ማበረታቻ ሊሰጣቸው የሚገባ መሆኑን አንድ በአንድ ተመልክቶ ካመነበት ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ሊወሰን ይችላል ፡፡

## አንቀጽ (14)

## የተሻረ መመሪያ

በኢንቨስተሮች ተሽከርካዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመወሰን በቦርዱ ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/1997 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## **አንቀጽ (15)**

## **መመሪያውን ስለማሻሻል**

የተሽከርካሪ ማበረታቻ መመያ እንዳስፈላጊነቱ በየጊዜው ሊሻሻል ይችላል ፡፡

መመሪያ ከጥር 5 ቀን1999 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል

አዲስ አበባ

------------------------------------

የፌዴራል ኢንቨስትመንት ቦርድ ሰብሳቢ

# <u>አባሪ</u>

## <u>ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀድላቸው</u>

## <u>የማምረቻ ኢንዱስትሪ የሥራ መስኮች</u>

ሀ/ <u>ጨርቃ ጨርቅና የልብስ ስፌት ኢንዱስትሪዎች</u>

1. የጨርቃ ጨርቅ ጭረቶችን መፍተል፣
2. የተፈተሉ የጨርቃ ጨርቅ ጭረቶችን መሸመን፣ ኒት ማድረግ፣
3. የተፈተሉ የጨርቃ ጨርቅ ጭረቶችን ፣ የተሸመኑና ኒት የተደረጉ ጨርቃ ጨርቆችን፣ ማንጣት፣ ማቅለም ፣ ማተም ወዘተ ።
4. የጨርቃጨርቅ አልባሳትን ማምረት ።

ለ/ <u>ሥጋ ፣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች</u>

1. ከቤትና ከዱር እንሰሳት እንዲሁም ከአዕዋፈት በቁራ ሥጋ ማምረት፣ የሥጋና ሥጋ ውጤቶቹን በፋብሪካ ማቀነባበር ።
2. ዓሣ፣ አዞ፣እና የመሳሰሉ እንሰሳት ሥጋዎችንና ውጤታቸውን በፋብሪካ ማቀነባበር ።
3. ቆዳን በመጨረሻ መልኩ (ክረስትን ጨምሮ) በፋብሪካ ማልፋት ።
4. የቆዳ አልባሳትን፣ የቆዳ ዕቃዎችን ( ቦርሳ፣ ቀበቶ፣ ጫማ ፣ ወዘተ.) ማምረት ።

ሐ/ <u>የአገሮ ኘሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች</u>

1. የቅባት እህሎችን፣እና ውጤቶችን  በፋብሪካ ማቀነባበር( አበጥሮ ማሸግን ብቻ የማክናወን ሥራን አይጨምርም) ።
2. ጥራጥሬ፣ እና ውጤቶችን በፋብሪካ ማቀነባበር(አበጥሮ ማሸግና ብቻ የማከናወን ሥራን አይጨምርም) ።
3. ፍራፍሬ ፣ አትክልት በፋብሪካ ማቀነባበር ።
4. ከእንሰሳት፣ ከአትክልት የምግብ ወይም ምግብ ያለሆኑ ቅባቶችን ማምረት።
5. ወተትና የወተት ውጤቶችን በፋብሪካ ማቀነባበር ።

6. እስታርች እና የስታርች ውጤቶችን ማምረት ።
7. የእንስሳት መኖ በፋብሪካ ማዘጋጀት ።
8. ስካ6ር ማምረት ።
9 ካካዎ፣ቸኮላታ፣ እና ስካ6ር የሚዘጋጅ ጣፈጭ ምግባችን ማምረት።
10. ማካሮኒ፣ ኑድል እና የመሳሰሎት ምግቦችን ማምረት ።
11. የጭረት ሰብል ውጤቶችን በፈብሪካ ማምረት ።
12. ጎማ፣ ሙጫ እና የመሰሰሎ የዛፍ ወተቶችን በፈብሪካ ማቀነባበር ።
13. ፀረ ተባይ ፣ ፀረ ሻጋታ ፣ፀረ አረም፣ እና መድሐኒት፣ሽቶ ለማምረት የሚውል ተክሎችን በፋብሪካ ማቀነባበር ( መሠረታዊ ዝግጅት መሆን ይኖርበታል ) ።
14. ድንች፣ እና ድንች መሰል የሥራ ሥር ተክሎችን በፈብረካ ቀነበቀበር።
15. ቡና ፣ሻይ በፈብረካ ማቀነባበር (ብናን አበጥሮ ማሸግን አይጨምርም)።
16. ቅመማ ቅመሞችን እና የቅመማ ቅመም ውጤቶችን በፈብሪካማቀነባበር (አበጥሮ ማሸግን ብቻ የማከናወን ሥራን አይጨምርም) ።
17. የወይን ጠጅ መጣል ።
18. ከብትል መጠጦችን መጥመቅ።
19. ማር እና የማር ውጤትን በፋብሪካ ማቀነባበር ።
20. ፐልሀ ማምረት ።

ቁጥር____________________

REF .No

በትግራይ ብሔራዊ ክልል ለኢንቨስትመንት ቢሮ

በአማራ ብሔራዊ ክልል ለኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ለኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

በአፋር ብሔራዊ ክልል ለኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

በደቡብ ብ /ብ /ህ/ ለኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

በጋምቤላ ህ/ ብ/ ክልል ለኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

በሶማሌ ብሔራዊ ክልል ለኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

በቤንሻንጉል ጉምዝ ብ/ ክ/ ለኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

በሐረር ብሔራዊ ክልል ለኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል ለኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>

የኢንቨስትመንት ቦርድ ኢንቨስተሮች <u>ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ</u> ለማስገባት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለማስተናገድና በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎችና ሎጆች የሚያስፈልጉ ለሚመሣሪያዎችና ዕቃዎች ከጉምሩክ ነፃእንዲገቡ ለመፍቀድ እንዲቻል ከሰኔ 11 ቀን 1988 አንስቶ በሥራ ላይ የሚውል መመሪያ አውጥተõል ፡፡

ስለሆነም ለአፈጻጸም እንዲረዳችሁ በማሰብ ከዚህ በላይ የተገለጹትን የቦርዱን መመሪያዎች ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆናችን እንገልጻለን ፡፡

ከሠላምታ ጋር

አባሪ ፣ 18 ገጽ

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለዋና ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
  ኢትዮÉያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን
  <u>አዲስ አበባ</u>፣

**በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎችና ሎጆች የሚያስፈልጉ ቋሚ መሣሪያዎችና ዕቃዎች ከጉምሩክ ነፃ እንዲገቡ ለመፍቀድ እንዲቻል በኢትዮÉያ ኢንቨስትመንት ቦርድ የወጣ መመሪያ**

የኢትዮÉያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የፍቀዱቱን የኢኮኖሚ ልማት ለማፈጠንና የሕዝቦቿን የኑሮ ደርጃ ለማሳደግ ኢንቨስትመንት ማበረታታትና ስፋፋት ሥራን አስፈላጊነት ትኩረት የሰጠው በመሆኑ የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 37/1988 እና ይህንኑ ለማስፈጸም የኢንቨስትመንት ማበረታቻ አሰጣጥ ደንብ ቁጥር 7/1988 ያወጣ በመሆኑ ፣

በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር 7/1988 አንቀጽ 15/ 1/መሠረት በኮከብ ደርጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎችና በፓርኮችና በታሪካዊ ቦታዎች ለሚቋቋሙ ሎጆች የሚያስፈልጉ ለምግብ ማበሰያና ማዘጋጃ እንዲሁም ለላውንደሪ አገልግሎቶች የሚውሉ ከፍተኛ ቋሚ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገባ በመፈቀዱ ፣

በዚሁ ደንብ አንቀጽ 15/2/ እንደተመለከተው ለባለኮከብ ሆቴልና ሎጅ ኢንቨስትመንቶች የሚያስፈልጉ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ዕቃዎች ዓይነትና ብዛት የፌዴራል መንግሥቱ የኢንቨስትመንት ቦርድ በመመሪያ በሚያወጣው ዝርዝር እንደሚወሰን በተደነገገው መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል ።

## ክፍል አንድ

## ጠ ቅ ላ ላ

1. እያንዳንዱ የሆቴል ፕሮጀክት ማበረታቻ ማግኘት የሚችለው የኢትዮÉያ ቱሪዝም ኮሚሽን ባወጣው የሆቴል ደረጃ መሰፈርት መመሪያ መሠረት የሆቴሎ ፊዚቢሊቲ ጥናትና ዲዛይን በቅድሚያ ታይቶ በኮከብ ደረጃ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል ተብሎ ሲታመንበት ይሆናል ።

2. ለእያንዳንዱ የሆቴልና ሎጅ ፕሮጀክት በቀረበው የፊዚቢሊቲ ጥናትና ዲዛይን መሠረት በቅድሚያ የተፈቀዱለት የምግብ ማዘጋጀና ሣብሰያ እንዲሁም የላውንደሪ ዕቃዎችና መሣሪያዎች ዝርዝር በመጨርሻ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲለቀቁ የሚደርግው ያስገባቸው ዕቃዎችና መሣሪያዎች በለሥልጣኑ ከቀረበው የሆቴል ወይም ሎጅ ዲዛይን እንዲሁም ከተሠራው ሕንፃ የውስጥ ክፍሎች ይዘት ጋር በማገናዘብ ለታለመላቸው አግልግሎት ሊውሉ እንዲሚችሉ በተጨባጭ ሲታመንበትና ለፕሮጀክቱ አስፈላጊ መሆናቸው በባለሥልጣኑ መ/ቤት ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል ።

3. የሆቴል ወይም የሎጅ ኘሮጀክቱ የሕንፃ ግንባታሂደቱ አልቆ የውስጥ መገልገያ ዕቃዎችና ፋሲሊቲዎች ተሟልተው የሆቴል አግልግሎት መስጠት ሲጀምር የቱሪዝም ኮሚሽን መሰፈርቶችን የማያሟላ ሆኖ በኮከብ ደርጃ መመደብ የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ በተፈቀዱለት ዕቃዎችና መሣሪያዎች ላይ በነፃ እንዲያስገባ የተነሳለትን የጉምሩክ ቀረጥ ለመንግሥት ገቢ ያደርጋል ፡፡

## ክፍል ሁለት

በኮከብ ደርጃ ለሚመደቡ ሆቴሎች በተጨማሪም በብሔራዊ ፓርኮችና በታሪካዊ ቦታዎች ለሚቋቋሙ ሎጆች ከቀረጥ ነፃ የሚፈቀዱ ከፍተኛ ቋሚ የምግብ ማዘጋጃና ማብሰያ ዕቃዎች ዓይነትና ብዛት ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ፡፡

1. MAIN KITCHEN HEAVY DUTY MACHINES AND UTENSILS

| No. | MACHINE/EQUIPMENT TYPE | Rooms 10-50 (Qty) | Rooms 51-100 (Qty) | Rooms 101& Above (Qty) |
|---|---|---|---|---|
| 1.1 Vegetables & Soups Preparation Section(Entremetier) | | | | |
| 1. | Peeling Machine: 125 Kgs per hour peeling capacity and above | 1 | 1 | 1 |
| 2. | Refrigerator or deep freezer: capacity 700 liters and above | 1 | 2 | 2 |
| 3. | Gas range(stove): 6 burner and above Dimension: 900X850 870 mm high and above | 1 | 2 | 2 |
| 4. | Electric range(stove): Equipped with 4 hot plates with each plate size of 300X300 mm square and above.Dimension:800X900X850mm high and above. Voltage: 3N/50hz/380 and above. | 1 | 2 | 2 |
| 5. | Deep-fat fryer-Electrical or gas or combined: Rated oil capacity 20 liters and above Demesion: 800 wideX400X850 mm high and above. Electric option: total power input 24 kw supply voltage 50hz 380 and above. | 1 | 1 | 1 |
| 1.2 COLD FOOD PREPARATION SECTION (GARDE-MANGER) | | | | |
| 1. | Slicing machine: Specification: gravity feed, blade diameter 9 inches and above: 2N/50260/380voltage | 1 | 1 | 1 |
| 2. | Universal Mixer(mixing machine)with vegetable preparation attachment: capacity: 30 litres bowl capacity and above with floor installation accessories | 1 | 2 | 2 |
| 3. | Refrigerator or deep freezer: Capacity: 700 litres and above | 1 | 2 | 2 |
| 4. | Food displayer cold unit: Dimension: 2100 length X 650 width X 900 mm height and above | 1 | 1 | 1 |
| 1.3 BUTCHERY SECTION | | | | |
| 1. | Meat mincing machine: Capacity 150 Kgs/hour and above | 1 | 2 | 2 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2. | Walk in cold room:<br>In galvanized steel finish constructed on the modular principle with each panel interlocked with its neighbour by special conterlock both exterior and interior surfaces are injected with urethane insulation forming a thickness of 100 mm. The freezer room provided with freezing system, door frames heater complete with transformers ,pressure relief valve dimension:<br>1440X2640X2150 h mm and above.<br>OR<br>Split freezing system, Hermetic compressor, capacity: 19m3: 3N/50/380 voltage and above including condesning unit, drain and refrigerant lines. | 1 | 2 | 2 |
| 3. | Refrigerator or deep freezer:<br>700 litres capacity and above | 1 | 2 | 2 |
| 1.4 HOT FOOD PREPARATION SECTION (SAUCER) | | | | |
| 1. | Hot food unit with gastronorm:<br>Three bain marie wells and above: voltage 3N/50-6/380:<br>Dim: 1200X650X900 mm and above | 1 | 2 | 2 |
| 2. | Food displayer hot unite:<br>Dimension 2100 wideX650 deep X 900 mm high and above | 1 | 1 | 1 |
| 3. | Refrigerator or deep freezer:<br>700 litres capacity and above | 1 | 1 | 2 |
| 4. | Standard Hot capboard (cabinet) for food<br>Dimenstion 940 length X 560 width X 965 mm height and above<br>2N50-60/380 voltage | 2 | 2 | 3 |
| 5. | Tilting bratt/frying tables electric:<br>Dimension 800 wide X 900 deep X 850 mm high and above; cast iron pan sis lid and sides. Electric power supply: 380V; Total power input 12 KW and above. | 1 | 1 | 1 |
| 6. | Grill Salamander:<br>Dimension 650 wide X 500 deep X 550 mm high and above. 3N/50/380 voltage | 1 | 2 | 2 |
| 7. | Gas range(stove):<br>Six burners and above<br>Dimension 900 wide X 850 deep X 870 mm high and above | 1 | 2 | 2 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 8. | Electric range(stove):<br>Equiped with four hot plates (300X300 mm each)<br>Demension 800X850X mm high and above | 1 | 2 | 2 |
| 9. | Kitchen canopy with fan or air conditioning<br>System: A commercial Kitchen type with balanced extraction/induction system fan motor 2kw;380v and above; including console. | 1 | 1 | 1 |
| | 1.5 STILL ROOM SECTION(HOT AND COLD BEVERAGES DISPENSING) | | | |
| 1. | Cold juice dispenser: with temperature control unit single container type 20 litres and above; twin container type 11+11 litres and above. | 1 | 1 | 1 |
| 2. | Coffee machine with grinding machine: 3 groups; boiler capacity 15 litres and above; 3N/50/60/380 voltage, loading capacity of 6.2 kw and above; grinding machine loading 0.3 kw and above. | 1 | 2 | 2 |
| | 1.6 Pastry& Bakery Section( patissler) | | | |
| 1. | Universal planetary mixing and kneading machine:<br>capacity of 30 litres bowel and above complete with whisk, beater and dough hook | 1 | 1 | 1 |
| 2. | Dough roller and divider machine: dough divider with a capacity of 18 pieces each round and 5kgs. And above; Dough roller Dimension of tray 506X508 mm and above. | 1 | 1 | 1 |
| 3. | Refrigerator or deep freezer 700 litres capapcity and above | 1 | 2 | 2 |
| 4. | Refrigerated pastry displayer:<br>Dimension: 2100 length X 650 width 900 height mm and above | 1 | 1 | 1 |
| 5. | Multifunctional convection oven:<br>Capacity: one shelf unit holding 6 grids G/N Div 60 mm and above 3N/50/380 voltage | 1 | 2 | 2 |
| 6. | Electrical balding oven with compartment: with two decks and above with a capacity of 2 baking plates per deck (upto 470X800); voltage 3N/50/380v; loading capacity 10.2 kw and above. | 1 | 1 | 1 |
| | 1.7 STEWARD SECTION (WASH-UP SECTION) | | | |
| 1 | Dish washing machine with racks:<br>Capacity: 1000 plates per hour and above, fully automatic and drying agent injector, s/s execution with drain pump; 3N/50/380v | 1 | 1 | 2 |
| 2 | Glass washing machine with racks: capacity: 400 pint tumblers per hour and above; fully automatic and drying agent injector with drain pump; 3N/50/380V | 1 | 1 | 2 |
| 3 | ice cube machine:<br>capacity: 68 kgs/day and above | 1 | 1 | 2 |

| 1.8 RECEIVING AREA AND MAIN STORE-SECTIONS(FOR DRY & COLD FOOD ITEMS STORAGE) | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Automatic freight scale- for receiving aren't Capacity of 100 kgs and above. | | | |
| 2 | Walk in cold room-for store: requirements are the same as item 1.3(2) above. | | | |
| 1.9 MACHINES AND EQUIPMENT USED IN COMMON FOR ALL SECTIONS IN THE MAIN KITCHEN | | | | |
| 1 | Central boiler (centralized steam & hot water distribution system) | | | |
| 2 | Stand by generator with transformer | | | |

Note: All machines and equipment listed above will-have the complete fittings and necessaries.

## ክፍል ሶስት

በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎችና በብሔራዊ ፓርኮችና ታሪካዊ ቦታዎች ለሚቋቋሙ ሎጆች ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚፈቀዱ ለላውንድሪ አገልግሎት የሚውሉ ከፍተኛ ቋሚ ዕቃዎች ዓይነትና ብዛት ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

## HEAVY DUTY LAUNDRY-MACHINES AND EQUIPMENT

| No. | MACHINE/EQUIPMENT TYPE | Rooms 10-50 (Qty) | Rooms 51-100 (Qty) | Rooms 101 & Above (Qty) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | Washer/extractor<br>Capacity per load: 23 kgs. Dry weight and or inner drum volume 230 litres and above. Heating: electric or steam option | 1 | 2 | 2 |
| 2. | Hydro extractor:<br>Capacity per load 14.5 kgs dry weight or inner drum volume-58 litres and above | 1 | 2 | 2 |
| 3. | Tumbler dryer<br>Capacity per load 14 kgs dry weight or inner drum Volume 350 litres and above. Heating alternative-electricity/steam/gas | 1 | 2 | 2 |
| 4 | Flat work ironer (ironing machine):<br>Roller length 1000 mm and roller diameter 200 mm and above. Ironing speed 3.5 meters per minute and above | 2 | 2 | 2 |

Note: all machines and equipment listed above will have the complete fittings and necessaries.

## ክፍል አራት

የፌዴራል ኢንቨስትመንት ቦርድ ይህን በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎችና ሎጆች ማበረታቻ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው ሊያሻሻል ይችላል፡፡

ይህ መመሪያ ከሰኔ 11 ቀን 1988 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

መለሰ ዜናዊ
የፌዴራል ኢንቨስትመንት ቦርድ ሰብሳቢ

ቁጥር ___________________

ቀን ___________________

ለ-------------------- ዞን/ልዩ ወረዳ/ መስተዳድር ም/ቤት
--------------------

ጉዳዩ፡- ለቋሚ ተክሎች የተሰጠውን የመሬት ኪራይ እፎይታ መመሪያ ስለመላክ፣

የክልሉ መንግሥት ኢንቨስትመንት ከማበረታታት አኳያ የተለያዩ ተግባራት ያከናወነና በማከናወን ላይ የማገኝ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚህም መሠረት በግብርናው ዘርፍ በተለይ በቋሚ ተክሎች ልማት የተሰማሩ ባለሀብቶችን በተለያዩ ሁኔታ ማበረታታት በማስፈለጉ ምርት እስኪያገኙ ድረስ ከመሬት ኪራይ እፎይታ እንዲያገኙ ተወስኗል፡፡ በመሆኑ ዝርዝር ሁኔታውን የያዘ 4 ገጽ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ የላክን ስለሆነ ይህ ሰርኩላር ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ የመሬት ኪራይ እፎይታ ማበረታቻ በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ እንድታደርጉ አስታውቃለሁ፡፡

"ከሠላምታ ጋር"

አባተ ኪሾ
ርዕሰ መስተዳድር

ግልባጭ፣

ለም/ቤታችን ኢኮኖሚ ዘርፍ
ለክልሉ ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት
ለክልሉ ግብርና ቢሮ
አዋሣ፡፡

## <u>በግብርናው ዘርፍ በቋሚ ተክሎች ልማት ኢንቨስትመንት ለሚሠማሩ ባለሀብቶች መሬት ኪራይ ዕፎይታ ማበረታቻ አሰጣጥ መመሪያ</u>

በዓለማችን አፋጣኝ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣትና የዜጐችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኑሮ ለማሻሻል የነባው ኢኮኖሚ ሥርዓት ተወዳዳሪ አልተገኘለትም፡፡

በነፃው የኢኮኖሚ ሥርዓት ከፍተኛ ሚና ያለው የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሲሆን አገራችንም የነፃ ኢኮኖሚ ሥርዓትን መከተል ከጀመረችበት ጥቂት አመታት ወዲህ የግሉን ሴክተር ለማጠናከር በርካታ የኢኮኖሚ ማሻሻያ እርምጃዎችን የወሰደች ሲሆን ከተወሰዱት የፖሊሲ ማሻሻያዎች ውስጥ ተሻሽሎ የወጣው የኢንቨስትመንት ፖሊሲ አንዱ ነው፡፡

ለአንድ አገር ዕድገትና ብልጽግና አመቺ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ያልታከለበት የሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት መሆን ብቻ የኢኮኖሚ ዕድገትን ስለማያመጣ የተመቻቸ  የኢኮኖሚ ፖሊሲ መኖር ወሳኝነት አለው፡፡በተለይም የግል ኢንቨስትመንትን በሰፊው የሚጋብዝ የተመቻቸ ፖሊሲ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በግል ኢንቨስትመንትን በአገር ውስጥ ባለሀብት ብቻ የሚደረግ የኢንቨስትመንት እንቅስቀሴ ብቻውን የተፋጠነ የኢኮኖሚ ዕድገት ማምጣት የሚያስችል የፋይናንስ አቅም ስለማይኖረው የውጭ ባለሀብቶችን በሰፊው ሊስብና ሊያሣትፍ የሚችል አመርቂ የኢንቨስትመንት ፖሊስ በሥራ ላይ ማዋል ለኢንቨስትመንት መስፋፋትና ማጎልበት ወሳኝነት አለው፡፡

በማዕከላዊው መንግሥት ከሚወጡ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሕጎች በተጨማሪ ክልሎች እንደየአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ኢንቨስትመንትን ለማሣብ የሚያወጡዋው ደንቦችና የሚያደርጉት ማበረታቻዎች ለግሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

በዚህ ረገድ እስካሁን በክልላችን የግሉን የኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ከተከናወኑት ዓበይት ተግባራት ውስጥ፣

- የመሬት አሰጣጥ ሥርዓት የተቀላጠፈ እንዲሆን ማድረግ
- ኢንቨስትመንትን የሚያጠናክሩ ደንቦችና ሕጎች ተግባራዊ መሆን
  እንዲሁም ባለሀብቶች ችግሮቻቸውንና የሥራ እንቅፋቶቻቸውን ለማስወገድ የሚችሉበት ነፃ የመወያያ መድረክ /የኢንቨስትመንት ፎረም/ መፈጠሩም የክልሉ መንግሥት ለግሉ ሴክተር ያለውን በጎ አመለካከትና ተቆርቋሪነት በጉልህ የሚያሣይ በመሆኑ ለክልሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋት የሚኖረው ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡

ወደፊትም ኢንቨስትመንትን የሚያበረታቱ ቀጣይነት ያላቸው የፖሊሲ ማሻሻያ እርምጃዎች በክልሉ መንግሥት የሚወሰዱ ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ በግብርናው ዘርፍ በቋሚ ተክሎች ልማት ኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የገጠር መሬት ኪራይ የእፎይታ ጊዜ ማበረታቻ እንዲሰጥ ተወስኗል፡፡

"ቋሚ ተክሎች" ተብለው የሚታወቁት ምርት ለመስጠት ከአንድ አመት በላይ ጊዜ የሚወሰድባቸውና በተከታታይም ምርት የመስጠት ባህርይ ያላቸው ቢሆኑም በዚህ መመሪያ "ቋሚ ተክሎች"ተብለው የተወሰዱት ምርት ለመስጠት ከሶስትና ከአራት ዓመት ዕድሜ በላይ የሚወስድባቸውን ተክሎች ማለት ሲሆን እነሱም እንደ ቡና፣ሻይ ቅጠል፣ቃጫ፣ፍራፍሬ፣ጎማዛፍ፣ሸንኮራ አገዳ፣ደን ወዘተ… የመሣሰሉትን ያጠያልላል፡፡

እነዚህ ቋሚ ተክሎች በአብዛኛው ለውጭ ገበያ በመቅረብ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ሲሆኑ ከውጭ የሚገባውንም ምርት በሀገር ውስጥ በመተካት የውጭ ምንዛሪ ወጪን ያድናሉ፡፡ የሥራ ዕድልም በመፍጠር ረገድ የቋሚ ተክሎች ልማት ከዓመታዊ ሰብሎች ልማት የተሻለና አስተማማኝ የሆነ የሥራ ዕድል የመፍጠር ባሕሪ አላቸው፡፡ከነዚህ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሻገር የደን መራቆትን በመተካትና የአፈር መሸርሸርን በመግታት ለተፈጥሮ ሀብትና አካባቢ መጠበቅ ያላቸው አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህን ልማቶች ለማካሄድ የሚጠይቀው የመነሻ ኢንቨስትመንት ወጪ ከፍተኛ ከመሆኑ በሻገር የመጀመሪያ ምርት ለመስጠት ሶስትና አራት ዓመት አጥጋቢ ምርት ለመስጠት ደግሞ ከዚያም በላይ ዓመታት የሚወሰድባቸው በመሆኑ ጊዜ የሚጠይቁ ናቸው፡፡

ከፍተኛ ወጪ የሚፈስባቸውና ቋሚም በመሆናቸው ለምርቶቻቸው የገበያ ዋጋ መዳከም ወይም ማሽቆልቆል ቢያጋጥማቸው እንደ ዓመታዊ ሰብሎች በቀላሉ ወቅታዊ ገበያ ወዳላቸው ልማቶች ለመቀየር ስለማያስችሉ ለኪሣራም ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

ስለዚህ በነዚህ ልማቶች ዙሪያ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንቱ ከሚሰጠው ጥቅም አንፃር ልዩ ማበረታቻ ማድረጉ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

በዚህ መሠረት እንደነዚህ ዓይነቱ ማበረታቻ የባለሀብቶችን አቅም በማሣደግ ለተጨማሪ ኢንቨስትመንት የሚያበረታታ በመሆኑ የመሬት ኪራይ እፎይታ ጊዜ እንድሰጣቸው ተወስኗል፡፡

የመሬት ኪራይ እፎይታ ጊዜ የተፈቀደላቸው ቋሚ ተክሎች ኢንቨስትመንት መስኮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. <u>ቡና ልማት ኢንቨስትመንት</u>

ቡና፣እንደዝርያው ሁኔታ ከተተከለ ከ3-4 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የመጀመሪያ ምርት መስጠት የሚጀምር ስለሆነ የመሬት ኪራይ የእፎይታ ጊዜው ለአራት ዓመት ይሆናል፡፡

2. <u>የፍራፍሬ ተክሎች ልማት ኢንቨስትመንት</u>

የፍራፍሬ ቋሚ ተክሎችን በተመለከተ የኢንቨስትመንት ኘሮጀክቱ በቀጥታ ሙሉ በሙሉ ለነዚህ ተክሎች ልማት ከሆነ፣

2.1 ብርቱካን፣ሎሚ፣አቦካዶ፣ማንጎ፣ዘይቱን፣ወይን እና ተዛማጅነት ያላቸው ተክሎች ልማት ለ6 ዓመት የመሬት ኪራይ እፎይታ ጊዜ ይሰጠዋል፡፡

2.2 ሙዝ፣ፓፓዬ፣ተዛማጅ ተክሎች ለ3 ዓመት

2.3 የሸንኮራ አገዳ ተክል፣ ለ4 አመት የመሬት ኪራይ እፎይታ ጊዜ የሰጣቸዋል፡፡

2.4 ከላይ የተጠቀሱ የፍራፍሬ ተክሎችን በተቀናጀ መልኩ ለሚያለሙት የእፎይታ ጊዜ በአማካይ ይወሰዳል፡፡

3. <u>የደን ልማት ኘሮጀክቶች</u>

የደን ልማት ለአካባቢው ጥበቃ ከፍተኛ ጠቀሜታ ስለሚሰጥ የመሬት ኪራይ የእፎይታ ጊዜው ለ20 አመት እንዲሆን በተጨማሪም ዝርያቸው ረጅም ጊዜ ለሚቆዩ የደን ዓይነቶች እንደኘሮጀክቱ ባህሪ እየታየ ወደፊት የሚወሰን ይሆናል፡፡ ኘሮጀክቱ የባህዛፍ ደን ከሆነ የእፎይታ ጊዜው 4 ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡

4.<u>የሻይ ልማት ኘሮጀክቶች</u>

ሻይ ቅጠል፣በተክሎ ባህሪ ምርት መስጠት የሚጀምረው ከተተከለ ከሰድስተኛው ዓመት ጀምሮ በመሆኑ የመሬት ኪራይ የእፎይታ ጊዜ የሚቆጠረው የመሬት ርክበክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ ነው።

5.<u>የመመሪያው ተፈፃሚነት</u>

5.1 የመሬት ኪራይ ማበረታቻ የሚያገኙ ኘሮጀክቶችን ገምግሞ ለሚመለከታቸው አካላት የማሣወቅ ኃላፊነት የተሰጣው ለኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ነው።

5.2 ይህ መመሪያ ተግባራዊ የሚሆነው በአሁኑ ጊዜ ፈቃድ ተሰጥቷአቸው ወደ ማምረት ደረጀ ላልተሸጋገሩና ወደፊት ፈቃድ ለሚሰጣቸው ኘሮጀክቶች ይሆናል።

የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች
ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት ሥራ ስሰፈጻሚ ኮሚቴ
ሰኔ 1990 ዓ.ም